የሰ/መ/ቁ. 22860

የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ - ነ/ፈጅ ብርሃኑ ወንደሰን

ተጠሪ፡- አቶ ካሣዬ ዘውዴ - አልቀረበም፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረ ሲሆን ለተጠሪ በሁለት የዱቤ ሰነዶች የውሃ ማሞቂያ መሸጡንና ተጠሪ ግን ለገዙት ዕቃ ዋጋቸውን ስላልከፈሉ የዕቃዎቹን ዋጋ ብር 44,930 /አርባ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሣ/ ብር እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ ተጠሪም ክሱን ክደው ተከራክረዋል:: ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በከሣሽና በተከሣሽ መሀከል የተደረገ የሽያጭ ውል አልቀረበም፡፡ የዱቤ ሰነዱ በፍ/ሕ/ቁ. 1685 መሠረት ተጠሪን አያስገድዳቸውም፡፡ የሽያጭ ውል ተያይዞ ባለመቅረቡም ውሉ በከሣሽና በተከሣሽ መሀከል አለ ለማለት አይቻልም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አቤቱታው በአጭሩ ሲጠቃለል ሽያጩ የተደረገው በዱቤ ሰነድ /Credit invoice/ ሆኖ ሣለ የዱቤ ሰነዱ ጋር የሽያጭ ውል አልተያያዘም በማለት ፍ/ቤቱ ክሱን ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡



ይህ ችሎትም ከዱቤ ሰነዱ በተጨማሪ ሌላ የሽያጭ ውል አልቀረበም በማለት ክሱ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆኑን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ለቀረበው ክስ ምንም ዓይነት ማስረጃ ስላልቀረበ ውሣኔው ስህተት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው ተጠሪ በዱቤ ሽያጭ የገዙትት ውሃ ማሞቂያ ዋጋ እንዲከፍሉ ነው፡፡ አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 2001/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው ውሃ ማሞቅያውን መግዛታቸውንና ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ሕጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሑፍ በምስክር፣ በሕሊና ግምት፣ በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሐላ ማስረዳት እንደሚቻል በፍ/ሕ/ቁ. 2002 ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንዲያስረዳ የሚጠበቅበት ተጠሪ በዱቤ የውሃ ማሞቂያ ገዝተው የተረከቡ መሆኑን ነው፡፡ የውሃ ማሞቂያ ሽያጭ ውል ደግሞ በተለየ ሁኔታ እንዲደረግ ወይም ውሉ ስለመደረጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ሕጉ የማያስገድድ በመሆኑ አመልካች ሽያጩ ለመከናወኑ ማንኛውንም ማስረጃ ማቅረብ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ሽያጭ ለመደረጉ የዱቤ ሰነድ /Credit invoice/ አቅርቧል፡፡ ይህ የዱቤ ሰነድ ግራ ቀኙ ተስማምተው እስከፈረሙት ድረስ የዱቤ ሽያጭ መከናወኑን ለማስረዳት በቂ ነው፡፡ ሕጉ ይህ አይነቱ ሽያጭ በጽሁፍ እንዲሆን ስለማያዝም ከዱቤ ሰነዱ በተጨማሪ ሌላ የጽሁፍ ውል እንዲቀርብ የሚጠየቅበት ምክያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ከዱቤ ሽያጩ ጋር የጽሁፍ ውል ባለመያያዙ ሽያጭ